

ነገረ ሥዕል ክፍል ፩

ሥዕል ምን ማለት ነው?

ዓይነቶቹስ?

በቅዱሳት ሥዕላት ዙርያ ተከታታይ ትምህርት

በታይለማርያም ሸመልስ

ማኅበረ ቅዱሳን ሥነ ሥዕል


5/9/2010 ዓ.ም.



http://ethioicons.wordpress.com/

ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላት

ታሪክ ፣ መንፈሳዊ ትርጉም ፣ የሊቃውንት አስተምህሮ እና ሌሎችም . . .



አዘጋጅ
ኃይለማርያም ሽመልስ
2007 ዓ.ም.

አሳታሚ እና አከፋፋይ
ማኅበረ ቅዱሳን
አዲስ አበባ ማእከል

ሥዕለ ቅድስት ኦርሴማ ኃይለ ማርያም ሽመልስ ካሣ

ሥዕለ ቅድስት ኦርሴማ



የቅድስት ኦርሴማ እና ቅድስት ኦርሴማ ተብለው የሚጠሩ ቅዱሳት ኪንስት የተጋድሎ ሕይወትና ሥዕሉ ፫ቸው

ከዘጋጅ
ኃይለ ማርያም ሽመልስ ካሣ

ማውጫ


- የስልጠናው ዓላማ
- የሥዕል ትርጉም
- የሥዕል ዓይነቶች
- በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ የሥዕል ዓይነቶች
- የቅዱሳት ሥዕላት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ
- የቅዱሳት ሥዕላት ታሪክ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች

1. የሥልጠናው ዓላማ

- ከዚህ ሥልጠና በኋላ አንድ ሰልጣኝ
  - የሥዕል ትርጉም አውቆ ማስረዳት ይችላል
  - ስለ ሥዕል ዓይነቶች በጥልቀት በማወቅ የተለያዩ የሥዕል ዓይነቶች ይለያል
  - በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ የተለያዩ ዓይነት ሥዕሎች ያውቃል
  - የቅዱስት ሥዕላትን ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረዳት ይችላል
  - የቅዱሳት ሥዕላት ታሪክ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚጠቀሙ ያውቃል

የሥዕል ትርጉም

- ‹‹ሥዕል›› በቁም መልክ፣ የመልክ ጥላ፣ ንድፍ፣ አምሳል፣ ንድፍ በውኃ፣ በመጽሔት፣ በጥልፍ፣ በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ ተጽፎ ከደብር፣ ከእብን፣ ከእጽ፣ ከማዕድን ታንጦ፣ ተቀርጦ፣ ተሸልሞ፣ አጊጦ የሚታይ የሚዳሰስ ነገር ነው።።›› *አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ*
- ዮሐንስ ዘደማስቆ የተባለ የምስራቅ አብያተ ክርስቲያን ሊቅ ደግሞ ‹‹***ሥዕል ውክልና ሲሆን በውስጡ የተመሰለውን (የተወከለውን) ባለቤት የያዘ፡ ነገር ግን ከተወከለው ከባለቤቱ ጋር ግን የተወሰነ ልዩነት አለው።።***›› በማለት ያብራራዋል።


ባለቤት
ሥዕል


የሥዕል ትርጉም . . .

❑ *ሥዕል ነጠላ ሲሆን ሥዕላት ደግሞ ብዛት ያመለክታል።*

- በአጠቃላይ ሥዕል እና የሥዕሉ ባለቤት ማለትም በሥዕሉ የተወከለው ባለቤት ተመሳሳይነትና ልዩነት አላቸው። ተመሳሳይነታቸው ከላይ እንደተገለጸው ሥዕል የአንድ ነገር መልክ፣ የመልክ ጥላ፣ ምሳሌ (አምሳል) ወይም ውክልና ቢሆንም በውስጡ ግን የተመሰለውን (የተወከለውን) ባለቤት የያዘ በመያዙ ነው።
- ይህ ሲባል ግን ከተወከለው ከባለቤቱ ጋር ግን የተወሰነ ልዩነት ያለው መሆኑን በመረዳት ነው። በሌላ አነጋገር የተሣለው ሥዕል ባለቤቱን ቢመስለውም ውክልና እንጂ ባለቤቱ አይደለም ማለት ነው።

እንዴት እንመለከታለን

- በመመልከት
- በማሰብ (Mental image)፡-
  - ሕልም







Figure 1: Based on Shepard & Metzlar's 'Mental Rotation Task'



Figure 2: Mental Rotation Task Based on Canonical Orientations

የሥዕል ዓይነቶች



በጊዜ

- ሥዕሎች በተሣሉበት ዘመን ሊለያዩ ይችላሉ።
  - ያለፉ፣
  - አሁን በቅጽበት የሚታዩ እና
  - ወደ ፊት የሚመጡ ሥዕሎች

በአውታር



- ሥዕሎች በተሣሉበት አውታር ሊለያዩ ይችላሉ::

  – ባለሁለት ልሙጥ/ የተፈለፈለ

  – ባለሦስት





በባሕርይ

- የሥዕሉ ባሕርይ ስንል ሥዕሉ የተሠራበት ባሕርይ ማለታችን ሲሆን፤ አንድ ሥዕል ደግሞ
  - ረቂቅ
    - ሕልም፣ ራእይ
  - ግዙፍ
    - የብር፣ የወርቅ፣ የወረቀት፣ የብራና፣ የጨርቅ፣ የድንጋይ ላይ ሊሆን ይችላል
  - ሕይወት ያለው
    - የሰው ልጅ ዘፍ 1፡26
  - ሕይወት የሌለው
    - የብራና ላይ ሥዕሎች፣ የኮምፒውተር ሥዕሎች
  - የሚንቀሳቀስ ወይም የማይነቀሳቀስ

በባለቤት

- የሥዕሉ ባለቤት የሥዕሉ ዓይነት ሊለያየው ይችላል
  - በጸታ
  - ሕይወት ያለው ወይም የሌለው
  - በቅድስና ደረጃው ወዘተ . . . ሊለያዩ ይችላል።

ምልክቶች /Sign and Symbols /

- ምልክቶች የተለያዩ ሀሳቦች፣ ነገሮች፣ ቦታዎች እና ቃላቶችን ሊወክሉ ይችላሉ::እነዚህ ምልክቶች ከሥዕል ዓይነቶች መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን በቀላሉ አንድን መልእክት ለማስተላለፍ ይረዳሉ::
- መልእክቱም ሥዕሉን (መለእክቱን) ባስተላለፈው እና በተተላለፈለት አካል ስለመልእክቱ የተወሰነ መግባባት (ስምምነት) ሊኖር ያስፈልጋል:: እንዲህ ከሆነ አንድ ምልክት (ሥዕል) አንድን ነገር ሊወክል እና መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል::

ምልክቶች /Sign and . . .

- እነዚህ ምልክቶች ደግሞ የአሣሣል ዘይቤያቸውና በሚያስተላልፉት መልእክት ሊለያዩ ይችላሉ። ከሥር ቀጥለን የተወሰኑ የሥዕል ምልክቶችን እንመልከት።
  - ማስተዋል የሚገባ ነገር ቢኖር አንድ ምልክት ከአንድ በላይ ምድብ ውስጥ ሊካተት ይችላል። በመሆኑም የምልክቱን ምድብን የሚወስነው የመልእክቱ ዓላም ነው።

የሥዕላዊ ምልክት ዓይነቶች

- **<u>አይኮግራም (Iconograms)፡</u>** እነዚህ ምልክቶች አንድ ነገር ገላጭ በሆነ ሥዕል የሚገለጡ ውክልናዎች ናቸው።።
- **<u>አይሶታይፕ (ISOTYPE)፡</u>** አይነት የተሰኙት ሥዕላዊ ውክልናዎች ማኅበረሰባዊ፣ የቴክኖሎጂ እና ሌሎች ውስብስብ ሀሳብን በሥዕል መልእክት የሚያስተላለፉ ምልክቶች ናቸው።።



https://en.wikipedia.org/wiki/File:Basic_by_Isotype.jpg




https://en.wikipedia.org/wiki/Isotype_(picture_language)

የሥዕላዊ ምልክት . . .

- **<u>ካርቶግራም (Cartograms)፡</u>** እነዚህ ደግሞ የአንድን አካባቢ መልክአ ምድራዊ የሚያመለክቱ ሥዕሎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሀገር ካርታዎች




- **<u>ዲያግራም (Diagrams)፡</u>** የተለያዩ ግንኙነቶችንና መስተጋብሮችን ለማስረዳት የሚጠቅሙ የሥዕል ዓይነቶች ናቸው፡፡ ዓይነታቸውም ብዙ



የሥዕላዊ ምልክት . . .


- **<u>አይዶግራም (Ideograms)፡</u>** እነዚህ ምልክቶች አንድን ሀሳብ የሚወክሉ ሥዕሎች ናቸው::





- **<u>ፎኖግራም(Phonograms)፡</u>**

እነዚህ ምልክቶች ደግሞ አንድን ድምጽ ለመወከል የሚጠቅሙ ሥዕሎች ናቸው::





- ✓ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች
- ✓ ፎኖግራም ውስጥ ፊደሎች ይካተታሉ::

ፊደሎች ሥዕል ናቸው

- የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች በሺዎች ዓመታት ያስቆጠሩ ጥንታዊ ፊደሎችን በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በቁፋሮ አግኝተዋል፡፡
- እያንዳንዱ ቃል ወይም ሀሳብ ለብቻው በሥዕል ይገለጥ ነበር
  - ሱሜርያውን፣ ጥንታዊ ግብጻውያን፣ ቻይናውያን እና ሌሎች ተጠቃሽ ናቸው
  - በዚህ ዓይነት አጻጻፍ አንድን ጽሑፍ ለማንበብ/ ለመጻፍ ብዙ ምልክቶችን ማወቅ ግድ ይላል፡፡
  - መስማት ለተሳናቸው እነዚህ የእጅ ምልክቶች ተጠቃሽ ናቸው

✓ **ሄሮግሊፊክስ (hieroglyphics)፡** አንድን ቃል የሚገልጹ ሥዕላዊ ምልክቶች ናቸው፡፡ ብዙ ሺ ቃላቶች የተለያዩ ነገሮች፣ ሀሳቦችን ይገልጹ ነበር፡፡

ሁሉንም ምልክቶች ለማጥናት ይከብድ ነበር፡፡




ፊደሎች ሥዕል . . . .



- የተወሰኑ ድምጾችን በሥዕል በመወከል ሁሉንም ቃላቶች በቀላሉ መግለጽ ተቻለ። 22 ሆሄያትን የያዙ ፊደሎች በሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች ተሰሩ።

- ✓ **እነዚህ ምልክቶችን ፊደል ይባላሉ።** አንድን ድምጽ አንድ ምልክት ይወክላል።
- ✓ በዚህ ደግሞ በእነዚህ ምልክቶች ሊወከል የሚችለው (በሥዕሎቹ ሊገለጥ) ነገር ገደብ አይኖርም ማለት ነው።




http://www.ancient-hebrew.org/inscriptions/135.html

የግብጽ ፊደል እና ሄሮግሊፊክስ







የአርመን ፊደሎች


THE EVOLUTION OF
ARMENIAN ALPHABET
PETROGLYPH
HIEROGLYPH
SYLLABIC
ALPHABETS

የቻይና ፊደሎች



መስማት ለተሳናቸው የእጅ ምልክት



- በአጠቃላይ ማንኛውም ዓይነት ምልክት ሥዕል ነው!!!!

በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ የሥዕል ዓይነቶች



በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ የሥዕል ዓይነቶች

- በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ **ሦስት ዓይነት ሥዕላት** ሲኖሩ እነዚህም **ቅዱሳት ሥዕላት፣ ርኩሳን ሥዕላት** እና **ዓለማውያን ሥዕላት** ናቸው።።
- በዚህ ጽሑፍ ስለቅዱሳት ርኩሳን እና ዓለማውያን ሥዕላት ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ እና በዘመናችን ከሚገኙ ሁኔታዎች አንጻር ምንነታቸው፣ ዓይነታቸውን እና ልዩነታቸውን በምሳሌ እናያለን።።

ቅዱሳት ሥዕላት

- ቅዱሳት የሚለው ቃል ደግሞ **«ቀደሰ»** ከሚለው የግዕዝ ግሥ ሲሆን ትርጉሙም ለየ፣ አከበረ፣ መረጠ ማለት ነው። ከዚህም በመነሳት ቅዱሳት ሥዕላት ለእግዚአብሔር የተለዩ፣ የተቀደሱ ፣ልዩ ፣ ምርጥ፣ ንጹሕ እና ጽሩይ የሆኑ የቤተመቅደሱ መገልገያ ንዋያተ ቅድሳት በመሆናቸው «ቅዱሳት» ተብለው ይጠራሉ።
  - የቅዱሳንን ታሪክ እና ማንነት በጊዜው ላልነበርን በመንፈስ ዓይን እንድናይ ስለሚያደርጉን፤
  - አንድም ሥጋዊውን ዓለም ከሚያንጸባርቁ ዓለማውያን ሥዕላት ፈጽመው የተለዩ በመሆናቸው፤ አንድም የቅዱሳን ቅድስና ሥዕላቱን ቅዱስ ስላሰኛቸው፤

ቅዱሳት ሥዕላት

- አንድም በሥዕላቱ አድሮ እግዚአብሔር ስለሚፈጽመው ገቢረ ተአምራት የተነሣ ሥዕላቱ «ቅዱሳት ሥዕላት» ተብለው ይጠራሉ።

- በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት ተብለው የሚጠሩት ሐዋርያዊ ትውፊትንና ቀኖናን ጠብቀው የሚሣሉ የቅዱስ እግዚአብሔር፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን መላእክት፣ የቅዱሳን ነቢያት፣ የቅዱሳን ሐዋርያት እና የሌሎች ቅዱሳን ጻድቃን ማንነት፣ ሕይወትና ታሪክ የሚያሳዩ እና የሚወክሉ ሥዕሎች ናቸው::

  - ዘጸ25፣18-22፤ 37፣7-9፤ዘጸ 26-31፤36፣8-35::

በመጽሐፍ ቅዱስ ስንት ዓይነት የተቀደሱ ሥዕላት አሉ?

- **የባህርይ ሥዕል (መልክ)**
- የእግዚአብሔር አብ መልኩ የሆነ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ ነው። ይህንንም በወንጌል እና በመልእክታት ሐዋርያት አስተምረዋል።
- ለምሳሌ በዮሐ ፡18 “በአባቱ እቅፍ ያለ አንዱ ልጁ ገለጠልን እንጂ ማንም እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም። “ በቆላ ፡15 ላይ ደግሞ “የማይታይ እግዚአብሔርን የሚመስለው “በዕብ ፡3 “እርሱም የከብሩ መንጸባረቅና የመልኩ ምሳሌ ሆኖ . . .” እንዲሁም በዮሐ 14፡8 “እኔና አብ አንድ ነን።”

መጻኢውን (ወደፊት የሚመጣውን) የማወቅ ሥዕል

- ይህ ሥዕል በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የሚገኝ በእግዚአብሔር ቸርነት ለነቢያትና ጻድቃን የተሰጣቸው ወደ ፊት ስለሚመጣው የማወቅ ሥዕል ነው።።
- እግዚአብሔር ወደ ፊት ሊመጣ ስላለው ሁኔታዎች በልቡ ውስጥ ያሉ ሥዕላት ሁለተኛው የሥዕል ዓይነት ነው።።
  - በማቴ 24 ላይ የተገለጹትን ሥዕላዊ ወደፊት የሚሆኑ ትንቢቶች፣ በእግዚአብሔር ሕሊና ውስት ያለ ወደ ፊት የሚመጡ ክንውኖች፣ በሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፉትና ያልተጻፉት ሕዝ2፡3፣

በምሳሌ (አምሳል) ወይም በአርአያ ያለ ሥዕል

- በመምሰል የሚገለጥ የሥዕል ዓይነት ነው። በሕያውነቱ፣ በገጽነቱ ወዘተ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ይመስላል። በኦሪት ዘፍ 1፡26 ላይ “ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን በመልካችን እንፍጠር።” ተብሎ እንደተጻፈ።
- ሆኖም ግን የሰው ልጅ (ሥዕሉ) እግዚአብሔር (ባለቤቱ) ነው ማለት ግን አይደለም።
- አንድ ልጅ አባቱ ሃይማኖተኛ ቢሆን እሱ ግን በሃይማኖት የማይኖር ከሆነ “ አባቱን አይመስልም” እንዲባል። ምንም እንኳን በደም ግባትና በዘረ መል (DNA) ቢመሳሰሉም።

የረቂቃን አካላት ሥዕል

- “ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፤ በዘመናትም የሸመገለውም ተቀመጠ፡ ፡ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ የራሱም ጠጉር እንደ ነጭ ሱፍ ነበረ፤ ዙፋኑም እንደ እሳት ነበልባል ነበረ መንኩራኩሮቹም እንደሚነዱ እሳት ነበሩ።።” ትንቢተ ዳንኤል በምዕራፍ 7-9
- በአካል የማይዳሰሱት ረቂቃኑ አካላት ባለቤት ሲሆኑ ለነቢያቱ የታያቸው ራዕያት ደግሞ ሥዕል ይሆናል።

ወደፊት ሊመጣ ስላለው ምሳሌ የሆነ ሥዕል

- እፀጳጦስ ዘሲና **የእመቤታችን** (ዘፀ3፡2)፣
- የመጀመሪያዪቱ ድንኳን ለኋለኛው እውነተኛ ድንኳን ምሳሌ እንደመሆናቸው (ዕብ፡9) ወዘተ . . . ።።
  - *እነኚህ ምሳሌዎች ሥዕል ሲሆኑ ባለቤቶቹ ደግሞ ትንቢቱ ሲፈጸም የተገኙ ናቸው።።*

ያለፉ ድርጊቶችን፣ ተአምራት ወይም በጎ ሥራዎችን

- በጎ ላደረጉ ቅዱሳን የአክብሮትና የምስጋና እንዲሁም ለርኩሳን (ክፉዎች) ደግሞ የውርደት የመታሰቢያ ሥዕል ነው።።
- ይህ ደግሞ ወደፊት ለሚመጣው ትውልዱ በጎ እንዲሠራ፣ እንዲለማመዱ እና ክፉውን እንዲጸየፍ ለማድረግ ነው።።
- ይህ ዓይነቱ ሥዕል በሁለት ይከፈላል።።

- 1 የጽሑፍ
- ‹‹እግዚአብሔርም ሙሴን ‘የአማሌቅን ዝክር ከሰማይ በታች ጨርሼ እደመስሳለሁና ይህን ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፉው፤ በኢያሱም ጆሮ ተናገር::’ አለው::›› ዘፀ 17፡14

- መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል ብለን የምንቀበለው በቀጥታ ያ ረቂቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በመመልከት ወይም በማንበብ ሳይሆን ረቂቁን (ሊታይና ሊዳሰስ የማይቻለውን) የእግዚአብሔርን ቃል በሆሄ ሥዕላት አማካኝነት ነው።
- አንድም ሆሄዎቹ (ፊደላቱ) በራሳቸው ረቂቃን አይደሉም ምክንያቱም
  - ይታያሉና፤
- ቅዱሳንም አይደሉም ምክንያቱም
  - ለምንፍቅና ሆነ ለርኩሰት የሚጠቀሙባቸው ሰዎች አለና፤ ራሳቸውን ችለው ትርጉም የላቸውም ምክንያቱም እንደየቋንቋው ትርጉማቸው ሊለያይ ይችላልና።

- ለምሳሌ “ሀ” የሚለውን ፊደል ብንወስድ እንደየቋንቋው የሚወክለው ቃልና ትርጉም ይለያያል። በአማርኛ ሲሆን “ህኧ/Ha” የሚለውን ቃል ሲወክል በእንግለዚኛ ደግሞ “ይኡ(ዩ)” የሚለውን ቃል ይወክላል።

- ከዚህ የምንረዳው ማንኛውም ሆሄ ወይም ፊደል በተፍጥሮው ወይም በባህርይው የሚወክለው ቃል የለም። ነገር ግን የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደባህላቸውና አስተምህሯቸው ያንን ፊደል የሚወክሉበትን ቃል ይመድባሉ እንጂ።

- በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው ሆሄያት ረቂቅ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃላትን ስለሚወክሉ ብቻ ያ የተፃፍው ዓረፍተ ነገር ወይም ፅሁፍ ቅዱስ እንዲሆን አስችሎታል። ስለዚህ “መጽሐፍ ቅዱስ (አብዛኛውን ጊዜ በጥቁር ቀለም) የተጻለ የሆሄያት ሥዕል ነው ማለት እንችላለን።”
- አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህንን በመረዳት መጻሕፍትን በሥርዓተ አምልኮ ጊዜ ምዕመኑ እንዲሳለሙ አክብሮት እንዲሰጡ እና እንዲሰግዱ ታዛለች። ፊል 2፡10

- ነገር ግን እኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፍባቸውን ሆሄያት ፈጥረውናል ብለን እንደማናመልካቸው ፤ ስንሰግድላቸውም ሆነ ስንሳለማቸው በውስጣቸው ለተወከለው ለረቂቁ ለእግዚአብሔር ቃል እየሰገድን እያሰብን መሆን አለበት።
- ቅዱሳት ሥዕላትንም እንሣለማቸዋለን፣ እናከብራቸዋለን፣ ስግደትንም እንሰግድላቸዋለን እንጂ አናመልካቸውም።

- 2 **በሚታዩ ነገሮች**
- ለመታሰቢያ የተቀመጡ ሥዕላት ናቸው፡፡ “እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ነገረው ‘ማጉረምረማቸው ከእኔ ዘንድ እንዲጠፋ፤ እነርሱም እንዳይሞቱ ለማይሰሙ ልጆች ምልክት ሆና ትጠበቅ ዘንዱ የአሮንን በትር በምስክሩ ፊት አኑር’ ሙሴና አሮን እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ፡፡” ዘኁ 17፡10
- ኢያሱ4፡20-24

ርኩሳን ሥዕላት (ጣዖታት)


- ርኩሳን ሥዕላት በመጽሐፍ ቅዱስ የሚባሉት በተለያዩ መልኮች የሚሣሉ ሆነው የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የሚቃወሙና በተቃራኒው ደግሞ የሰይጣንን ክፉ ተግባራት የሚያወድሱት በሙሉ ናቸው።።
- በዚህ ዘመንም የጣዖት አምላኪዎች የሚጠቀሙባቸው ሥዕሎች፣ የአምልኮ ምልክቶች እና ጽሑፎች እና ወዘተ. . . ከዚህ መደብ ይገባሉ።።

ርኩሳን ሥዕላት (ጣዖታት)

- በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኙ ርኩሳን ሥዕሎች መካከል እስራኤላውያን በጥጃና በተለያዩ እንስሳት ምስል ሰርተው ያመልኳቸው የነበሩት ዘፀ 32፡1-10፤ ናቡከደነጾር በባቢሎን አውራጃ በዱር ሜዳ አቁሞት የነበረው ከወርቅ የተሠራ ምስል ዳን 3፡1፤ እና
- ከነዓውያን ያመልኳት የነበረችው « አስታሮት» የተባለችው የሴት ምስል ወዘተ. . . የመሳሰሉት ርኩሳን ሥዕላት ተብለው ይጠራሉ። እነዚህን ርኩሳን ሥዕላት ተብለው ለመጠራታቸው ዘዳ 7፡25፤ ነኛ ነገ 12፡28-30፤ ዳን ፲፡31፤ 12፡11፤ ማቴ 24፡15-18 መመልከት ይቻላል።

— ማንችስተር ዩናይትድ ዓርማ

ርኩሳን ሥዕላት (ጣዖታት)



ርኩሳን ሥዕላት (ጣዖታት)

ማንችስተር ዩናይትድ ዓርማ ላይ የሚታየው የሰይጣን ሥዕል



ዓለማውያን ሥዕላት

- ዓለማውያን ሥዕላት የሚባሉት ደግሞ መንፈሳዊ ይዘት የሌላቸው ማንኛውም ዓይነት ሥዕላት ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሥዕላት በሕዝበ እስራኤል ሆነ በጣዖት አምላኪዎች በአረማውያን ዘንድ ለአምልኮ የማይጠቀሙባቸው ሥዕላት ናቸው፡፡
- እነዚህ ሥዕላት ለዕለት ከዕለት ኑሯቸው የሚጠቀሙባቸው ሥዕሎችን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ በተለያዩ ዘመናት በተነሡ ነገሥታት በተሠሩ ሳንቲሞች ላይ የምንመለከታቸው የነገሥታት ሥዕሎች ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው፡፡
  - ማቴ 22፣20

- ወዳለንበት ዘመን ስንመልሰው ደግሞ ዓለማውያን ሥዕላት የሚባሉት ማንኛውም ዓይነት የሚታይና ወካይ የሆነ ነገር ግን ለአምለኮ የማይውል ሥዕሎችን በሙሉ ሚያካትት ነው።
- ለምሳሌ የተለያዩ አካላት ፎቶዎችን፣
  - ተንቀሳቃሽ ምስሎች(ቢንቀሳቀሱም የብዙ ሥዕሎች ውጤት በመሆናቸው)፣
  - የማንኛውም ቋንቋ ፊደላት (ሆሄያትም ቢሆኑ በእጅ የሚጻፉ ሥዕሎች ናቸው)፣
  - የተለያዩ አካላት አንድን ሀሳብ ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸው ውክልና ምልክቶች (የትራፊክ ምልክቶች፣ የድርጅቶች ዓርማ፣ ወዘተ. . .)፣
  - የለተለያዩ የመዋብያና ማስጌጫ ጌጣጌጦችን (ንቅሳትን፣ በእቃዎች ላይ የሚታዩ ሐረጋትን ወዘተ. . .) ያጠቃላል።







ቅዱሳት ሥዕላት ታሪክ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች

በሥነፍጥረት

- በኦሪት ዘፍጥረት ፩፤26 “ሰውን **በመልካችን** እንደምሳሌያችን እንፍጠር።።”
- በማቴዎስ ወንጌል 22፣20 “**ይህች መልክ** የማን ናት?”

  በመልካችን እና ***ይህች መልክ*** በጽርዕ ቋንቋ ሲተረጎሙ ***“ኤኢኮን”*** እና ***“ኢይኮን”*** በሌላ ትርጉሙ ***ሥዕል*** ይሆናሉ።።
- ያን አዳምን በአርአያህ የምትፈጥረውን **መልኩን** አሳየንና የእርሱን መልክ አይተን **የአንተን መልክ** እንድንጠግብ አሉት።። *መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ ኤጲፋኒዮስ*


በሥነፍጥረት. . .

- “የእግዚአብሔር ምስልና መልክም ከምንም ነገር ጋር ስለማይነጻጸር ሰውም ይህ **እውነተኛ መልክ መልኩ** በመሆኑ ከሌሎች ምድራዊ ነገሮች ጋር አይቀላቀልም” *ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ*
- የሰው ልጅ ‹‹የእግዚአብሔር መልክ የተሣለበት በምድር ላይ ያለ ሕያው የእግዚአብሔር *ሥዕል* ነው።።›› “human kind is the living icon of God’’ *ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን*
- **የመጀመሪያው ሠዓሊ** ፈጣሪ ዓለማት ቸሩና ኃያሉ አምላክ **እግዚአብሔር** ሲሆን **የመጀመሪያው *ሥዕል*** ደግሞ **ሰው** ነው።።

በዘመነ ብሉይ ኪዳን

- ‹‹የስርየት መክደኛ ስራ ፣ **ሁለት ኪሩቤልን ከተቀጠቀጠ ወርቅ ስራ፣** በምስክሩ ታቦት ላይ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል መክደኛውም ላይ ሆኜ አነጋግርሃለሁ::›› **ዘጸ25፣18-22፤ 37፣7-9**
- በቅድስቲቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መለያ በሆኑት መጋረጃዎች “ብልህ ሠራተኛ እንደሚሠራ ኪሩቤልን አድርጉባቸው” **ዘጸ 26-31፤36፣8-35::**
- **እግዚአብሔር ማዘዝ ብቻ ሳይሆን በጥበብና በማስተዋል መንፈሱን እንደመላባቸው**
  - የኡሪ ልጅ **ባስልኤል**
  - የአሂዳምኒክን ልጅ **ኤልያብን**

ዘጸ 31:1-6



SOLOMON'S TEMPLE

Solomon began to build "the house of the LORD" in Jerusalem on Mount Moriah in the spring of 967 or 966 B.C. (1 Kings 6:1; 2 Chron. 3:1–2) and completed it seven years later, in the fall of 960 or 959 B.C. (1 Kings 6:38). The temple itself, not including the surrounding chambers on three sides, was 90 feet (27.4 m) long, 30 feet (9.1 m) wide, and 45 feet (13.7 m) high. It resided in the middle of a court with boundary walls.

የሰሎሞን ቤተመቅደስ

በዘመነ ሐዲስ ኪዳን

በወንጌል

- ‹‹ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እንዲሁ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል።።›› ዮሐ 3፣14
- ጌታችን በምኩራብ ሲያስተምር ሆነ በቤተመቅደሱ ውስጥ የማይገባ ሥራ ሲሠሩ የነበሩት ሰዎችን ገርፎ ሲያወጣ በቤተመቅደሱ ውስጥ የነበሩትን ሥዕለ ኪሩብን አልተቃወመም አላስወጣም።
- ተአምረ ኢየሱስ ላይ ሥዕሎቹን ሕይወት እንደዘራባቸው ተጽፎ ይገኛል።

በትውፊታዊ መረጃዎች

- ወንጌላዊው ዮሐንስ በዕለተ አርብ አይሁድ እንደሰቀሉት ጌታን የሣለው ሥነ ስቅለት
- ‹ቅዱሱ ፊት›› (The holy face) ‹‹ ዘተገብረ ዘእንበለ እደ ሰብእ፣ ያለ ሰው እጅ የተሰራ ቅዱስ ሥዕል›› የተሰኘው የጌታ ሥዕል
    - አብጋር የዑር ንጉሥ
    - ቬሮኒካ 12 ዓመት ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት
- በግሪክኛ ቬራ(Vera) = እውነተኛ ኢኮና (Icona) = ሥዕል ማለት ነው። ስለዚህም ቬሮኒካ (Veronica) የሚለው እውነተኛ ሥዕል (True Icon) ማለት ይሆናል።
    - ያሣለችው የነሐስ ሥዕል አውሳብዮስ እንደተመለከተ ተናግራል።

ቬሮኒካ







https://en.wikipedia.org/wiki/Veil_of_Veronica

በትውፊታዊ መረጃዎች. . .

- ጲላጦስ ለጢባሪዮስ ቄሳር ስለ ጌታና እናቱ ድንግል ማርያም የላከለት ደብዳቤ
- የእመቤታችን ሥዕልም ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ሥሏታል

“ሰላም ለሥዕልኪ እንተ ሠዓላ በእዱ ሉቃስ ጠቢብ እም ወንጌላውያን አሐዱ።”

“መልክዐ ሥዕል”

- በግብጽ (ቅብጥ/ Copt) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትውፊት መሠረት ቫን ሴሉብ (Van Celub) የተባለ የታሪክ ምሁር በአሌክሳንድሪያ በሚገኝበት ወቅት በወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የተሣለ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ሥዕልን እንደተመለከተ ይናገራሉ።

የእመቤታችን መልክ


- እመቤታችን በሥጋ ምን ትመስል እንደነበር ቅዱስ ኤፊፋንዮስ በግልፅ እንዲህ አለ፦ "እመቤታችን በሁሉም ርምጃዎቿ ጎበዝና የተከበረች ነበረች፤ የምትናገረው በጣም ጥቂት ሲሆን ርሱም ለማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ብቻ ነበር፤ በጣም ዝግጁ ሆና የምትሰማና በቀላሉ ንግግር ለማድረግ የምትችል ናት፤ ለእያንዳንዱ ሰው አክብሮትና ክብር (ሰላምታ) ትሰጣለች፤ ቁመቷ መካከለኛ ሲሆን አንዳንዶች ግን ቁመቷ ከፍ ያለ እንደነበር ይናገራሉ፤ ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ያለምንም ፍርሐት በግልፅነት ያለምንም ሣቅና መጫጫኽ ትናገራለች፤ በተለይ ፈጽማ ለቁጣ የምትጋበዝ አልነበረችም፤ መልኳ እንደ ደረሰ የስንዴ አዝመራ ያማረ ጸጉሯ ቀይማ ነው፤ ዐይኖቿ ብሩሃትና የዋሃት የሆኑ ቀለማቸውም ፈዘዝ ያለ ቡናማ ሆኖ የዐይኖቿ ብሌኖች የዘይት-አረንጓዴ ይመስላል፤
- የዐይኖቿ ቅንድብ (ሽፋሽፍት) ከፊል ክብና ደማቅ ጥቁር ናቸው፤ አፍንጫዋም ረዥም፣ ከናፍሮቿ ቀይና ምሉዕ ሲሆኑ በቃሎቿ ጣፋጭነት የተመላባቸው ነበሩ፤ ፊቷ ክብ ሳይሆን ግን እንቁላልማ ቅርጽ ነበረው፤ እጆቿ ረዥምና ጣቶቿም በጣም ረዣዥም ነበሩ፤ ከማንኛውም ያልተገባ ኩራት ሙሉ በሙሉ የነጻች ስትሆን ግድየለሽነት ፈጽሞ ጨርሶ የለባትም ነበር፤ የሚመጡትን ነገራት በፍጹም ትሕትና ትቀበል ነበር፤ ተፈጥሯዊ ቀለማት ያላቸው (ማለትም በቤት ድር የተሠሩ) ልብሶችን ትለብስ ነበር፤ ይህም በእጅጉ አብሯት የሚሔደው አለባበስና ይህ እውነታ በራሷ ላይ በምታደርገው ቅዱስ ልብስ አሁን ቅሉ ሊረጋገጥ የሚችል እውነታ ነው፤ ለማጠቃለል ያህል በመንገዶቿ ሁሉ በመለኮታዊ ጸጋን የተመላች ነበረች።





Rome, Catacombs of Priscilla – Our Lady with the Prophet

ቅዱሳት ሥዕላት በቤተክርስቲያን



ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጀምሮ እስከ ጉባኤ ኬልቄዶን

- የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በዘመኑ በነበሩት ዓላውያን ነገሥታትና መኳንንት ፊት እየቀረቡ ስለሃይማኖታቸው በግፍ ሰማዕትነት ተቀብለዋል።
- የቀሩት ደግሞ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ክርስትና ይፋ እስከሚፈቀድበት ጊዜ ይኖሩ የነበሩት በግበበ ምድር ወይም ዋሻ ካታኮምብ (catacomb) ፈልፍለው ነበር።

ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .

- በዚህ ጊዜም የክርስትና ትምህርትን በመጽሐፍ አብራርቶና አስፋፍቶ መስጠት ከባድ ነበር።ምክንያቱም ፡-
  - ❖የሃይማኖት ነጻነት አለመኖር
  - ❖መጻሕፍት በብዛት ተዘጋጅተው ለምዕመናኑ መድረስ ያለመቻል
  - ❖የማንበቢያ ጊዜ እና ቦታ እጦት
  - ❖አብዛኞቹ አማኞች ከጣዖት አምልኮ የመጡና ማንበብና መጻፍ የማይችሉ (ያልተማሩ) መሆን
  - ❖በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሱትን አንዳንድ ታሪኮችን ለማስረዳትም ከባድ ስለነበር
- **ከዚህ በመነሳት በዚያ ዘመን የነበሩ የቤተክርስቲያን መሪዎች ቅዱሳት ሥዕላትን መጠቀም ፈቀዱ።**



Ceiling of Cubiculum in the Catacomb of Ss. Pietro and Marcellinus

ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .

<u>የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች</u>

- ቅዱሳት ሥዕላቱም በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘንድ የሚሣሉትም በምሳሌነት (symbol) ሲሆን የሚሣሉትም **በከሰል እና በአመድ** ነበር።
- ጌታችንም በስፋት በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘንድ በምሳሌ ወይም በውክልና መልኩ ተደርጎ ይሣል ነበር

To hear the Gospel is permitted to all: but the glory of the Gospel is reserved for Christ's true children only… for the glory is enlightening for those who believe, and blinding for them that believe not… [Therefore] many things we often speak in a veiled way, that the believers who know may understand, and they who know not may get no hurt.

ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .

- ለምሳሌ በዋሻው ፊት ላይ (አፈ ጽዮን) **“መልካሙ አረኛ” ዮሐ 10፡11**
  - *ይህ ሥዕል ላይ እረኛው የሚወክለው የክርስቶስ ጠባቂነት፤*
  - *በጎቹ ደግሞ እርሱ ያዳነቸውን ነፍሳት*



Catacomb of Callixtus



The Catacomb of Domitilla



Catacomb of Priscilla：
https://en.wikipedia.org/wiki/Catacomb_of_Priscilla

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች . . .

- እነኚህ ክርስቲያኖች ሲገናኙ ክርስቲያን መሆናቸውን የሚገልጽ በተጨማሪም ክርስቲያናዊ እምነታቸውን በትክክል የሚገልጥ ምስጢራዊ ምልክት (secret code) ወይም ጎቡዕ መለያ (secret identity) በሥዕል ይጠቀሙ ነበር።
- የዚህ ምስጢራዊ ምልክት ወይም ሥዕል “**የዓሣ” ሥዕል** ነበር። ሥዕሉንም በከንዳቸው ይነቀሱት ነበር።
- በግሪክ “ዓሣ” ማለት “**ΙΧΘΥΣ** ወይም **ኢ**ᎇ**ቱስ**” ማለት ሲሆን እያንዳንዱ ሆሄ ሲተነተኑ
    - “**Ι**ήσους **Χ**ρίστος **Θ**έου **Υ**ίος **Σ**ώτηρ
    - **J**esus **C**hrist **S**on of **G**od, **S**aviour
    - **ኢ**የሱስ **ክ**ርስቶስ **ወ**ልደ **እ**ግዚአብሔር **መ**ድኀን”

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች . . .







የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች . . .

- በበግ ምሳሌ ተሥሎ ይገኛል ፡- ዮሐ 1፡29



ዘላለማዊነቱን ለመግለጽ



ሥዕል3 በ4ኛው መ.ክ.ዘ የተሣለው በኮሞዲላ (comodilla) የሚገኘው ካታኮምብ ውስጥ የሚገኘው **የጌታችን ሥዕል**

- አልፋና አሜጋ
  - የክርስቶስን መጀመሪያነትና ፈጻሚነትን ለመወከል የሚጠቀሙበት የፊደል ሥዕል





ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .

- በምሳሌ ከመሣል በተጨማሪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በተገለጠበት ወቅት የፈጸማቸውን ተአምራት በሥዕል ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ይገልጡ ነበር፡፡
    - ለምሳሌ የምሴተ ሐሙስ ሥዕል



ከሐዋርያት ጋር 350 ዓ.ም በሮም ካታኮምብ
(Catacomb of St. Domitilla) የግድግዳ (fresco) ላይ ሥዕል

መጻጉዕን ሲፈውስ



- 12 ዓመት ደም ይፈሳት የነበረችውን ሴት ሲያድናት



- የጌታችን ታአምራትን ከብሉይ ታሪኮች ጋር በማዛመድ ምስጢርን ያስተምሩ ነበር።።



ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .

- ከብሉይ ኪዳን ታሪኮች
  - ታሪኮቹም ተአምራታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያካትታሉ
  - *ለምሳሌ የቀደሙት ሰዎች አዳምና ሔዋን እንዴት እደሳቱ ያሳታቸውም እባብ በመካከላቸው እንዳለ ሆኖ ይሣል ነበር።*



- የነቢዩ ሙሴ ከዐለት ውኃ ሲያፈልቅላቸው



ነቢዩ ኖኅ



Rome, Catacombs of Sts. Marcellinus and Peter – Noah in the Ark

ነቢዩ ዮናስ



Rome. Catacombs of Sts. Marcellinus and Peter – Jonah is vomited out


ሠለስቱ ደቂቅ



Rome, Catacombs of Priscilla – three children in the furnace

ነቢዩ ዳንኤል





ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .

- ከሐዲስ ኪዳን ታሪኮች በሥዕል ከተገለፁት መካከል
    - ብሥራተ ገብርኤል፣
    - ጌታ በቤተልሔም መወለድና ሰብአ ሰገል መጥተው መስገድ፣
    - ጥምቀትና የሦስት ዓመት ከሦስት ወር ትምህርት ከተአምራት ጋር፣
    - እመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ በግራዋ ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ አርሷ እያመለከተ፡-***“ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልደ ወልደ”*** ያልኳት እርሷ ናት፣. . . .

ሥዕላዊ ምልክቶች በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች

- ከጌታችን ምሳሌዎች በተጨማሪ ክርስቲያኖች በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት የተለያየ ምልክቶችን ይጠቀሙ እና እምነታቸውን ይገልጹ ነበር። ከእነዚህ መካከል
  - የቄወራ ቅጠል ያያዘች ርግብ፡- ሰላም ያገኘችን ነፍስን ትመሰላለች።



Catacombs of Domitilla, Rome



- መልሕቅ፡- ወደ ሰላምና የጸጥታ ወደብ መንግሥተ ሰማያት የደረሰች ነፍስን ያሳያል







- ዓሣ፡- የክርስቲያኖች ምሳሌ ጭምር ነው፡፡
  - *‹‹እኛ ትንንሽ ዓሦች ነን፡፡ ልንድንም የምንችለው ውኃ ውስጥ ብቻ እስከ ሆንን ድረስ ነው፡፡››*
  - ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም ይወክላል





- ጣዎስ፡- ከዘለዓለማዊ ሕይወት ጋር ይያዛል





የጆን ካልቪን አስተምህሮ እና አመለካከት እውነት ወይስ . . .

- በቅ.ሥዕላት እና በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የነበረው የ John Calvin እና የተከታዮቹ የተሳሳተ አስተሳሰብ በ20ኛው መ.ክ.ዘ በተገኙ አዳዲስ የአርኪዮሎጂ ግኝቶች (ቁፋሮዎች) ስሕተት መሆኑ ተረጋግጧል።
- አሁንም ቢሆን ብዙ አዳዲስ የሆኑ ማስረጃዎች በአርኪዮሎጂካል (መሬት ቁፋሮ) ዳሰሳዎች ወይም ፍለጋዎች እየተገኙ ናቸው።
- በመሆኑም በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እና በአይሁዶች መካከል የነበረው ሰፊ የቁሳዊ ማስረጃ (physical evidence) ቀዳዳ ከመካከለኛው ምስራቅ፣ ከደቡብ እና ከምስራቅ አውሮፓ እና ሰሜን አፍሪካ በተገኙ ብዙ ግኝቶች በአሁን ሰዓት እየተደፈነ ነው።

የጆን ካልቪን አስተምህሮ እና አመለካከት እውነት ወይስ . . .

- በቁፋሮ ከተገኙት ግኝቶች በጣም አስደናቂው እና ተዋቂው የጥንታዊቷ ዱራ አዩሮፓስ (Dura Europus) ከተማ ግኝት ነው።
- ይህች ከተማ የምትገኘው የነበረችበት ቦታ በአሁኑ ሰዓት ሶሪያ በምትባለው ሀገር ምዕራባዊ ወሰን አካባቢ ነበር። ከተማዋ እንደገና የተገኘችው በተመራማሪዎች በ1920 ዓ.ም እ.ኤ.አ ነበር።
- በሮማውያን አገዛዝ ሥር ሳሉ የከተማዋ ነዋሪዎች ከተማዋን በ256-257 ዓ.ም በሳሳንያን ሲይጅ (sassanian siege) በተባለው ጦርነት ምክንያት ከተማዋን ትተዋት ተሰደው ነበር።

❑ ***ይህ ደግሞ በ20ኛው መ.ክ.ዘ. ለነበሩ እና በዚህ ዘመን ላሉ አርኪዮሎጂስቶች ከተማዋ ብዙ ጉዳት ሳይደርስባት በጥሩ ሁኔታ ተጠብቃ እንዲያገኟት ምክንያት ሆኖአቸዋል።***


የጆን ካልቪን አስተምህሮ እና አመለካከት እውነት ወይስ . . .

- ይህች ከተማ ለተለያዩ የእምነት ተቋማት (ለምሳሌ **ክርሰቲያኖች ፣ ለአይሁድ፣ ለጣዖት አምላኪዎች** ወዘተ....) መናኸሪያ ነበረች ።
- ትኩረታችንም በከተማዋ በምትገኘው **የቤት ቤተክርሰቲያን** ነው። የግል ቤቶች ቅድመ ቆስጠንጢኖስ (pre Constantine) ለሥርዓተ አምልኮ እና ሌሎች የአካባቢው ማኅበረሰብ ያገለግሉ ነበር።
- ይህች የቤት ቤተክርስቲያን በቁፋሮ እስከ አሁን ከተገኙት ረጅም እድሜ ያስቆጠረችው ቤተክርስቲያንን ስትሆን በ233ዓ.ም ገደማ እንደነበረች ጥናቶች ያሳያሉ።

የዱራ ኢሮፖስ ቤተክተርስቲያን በቁፋሮ እስከ አሁን ከተገኙት ረጅም እድሜ ያስቆጠረችው ቤተክርስቲያን።




የቤተክርስቲያኑ የውጭ ፍርስራሽ



የቤተክርስቲያኑ መሰረት ፕላን


የዱራ ኢሮፖስ ቤተክተርስቲያን የመጠመቂያው /baptistery/ክፍል በከፊል።




በቤተክርስቲያኗ መጠመቂያ ክፍል ከሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላት

- ከመጠመቂያው ገንዳ በስተኋላ ከመጠመቂያው ገንዳ እና ጣራ መካከል የሚገኘው ግድግዳ ላይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ **“መልካሙ እረኛ”** ሥዕል ሲኖር ከሥዕሉ ሥርም አዳም እና ሔዋን ተሥለው ይገኛሉ።
- በመጠመቂያው በደቡብ ግድግዳ ላይ ሳምራዊቷ ሴት ዮሐ4 4-26 ከዚህ ሥዕል በስተገራ ደግሞ የነቢዩ ቅ/ዳዊት ከጎሊያድ ጋር ሲዋጋ
- በሰሜን የመጠመቂያው ግድግዳ የሽባዎች (መፃጉ) ፈውስ የሚያሳይ በማር 2፡1-2
- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና የቅዱስ ጴጥሮስ በውሃ ላይ መሔዳቸውን የሚያሳይ ሥዕል እነኚህ እና ሌሎች. . . ሥዕሎችም በቤተክርስቲያኗ ተገኝተዋል።

በቤተክርስቲያኗ መጠመቂያ ክፍል ከሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላት መካከል



ሳምራዊቷ ሴት



የጆን ካልቪን አስተምህሮ እና አመለካከት እውነት ወይስ . . .

- የክርስቲያኖቹ የአምልኮ ቦታ ብቻ አልነበረም በቅ/ሥዕላት ያሸበረቀው የአይሁድ ቤተ መቅደስም ጭምር እንጂ ለምሳሌ ያህል
  - **የነቢያት ሥዕል** የአብርሐም፣ የሙሴ፣ የዳዊት፤
  - **ምልክቶች** ፡-ሚኖራህ (menorah) ፣ቶራህ ጥቅል(ብራና) (torah scroll)፤
  - **ድርጊቶች** እንደ ይስሐቅ ሊሰዋ ሲቀርብ፣ ሙሴ አስርቱን ትእዛዛትን ሲቀበል ወዘተ... ያሉት በቤተ-መቅደሱ ተገኝተዋል።

ቅዱሳት ሥዕላት ከመጀመሪያዎቹ. . .


- ክርስትና በቅድስት እሌኒ ልጅ ታላቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በአዋጅ የግሪኮ ሮማን (Greeko –Roman) ግዛት በ313ዓ.ም ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ በታወጀበት ወቅት ስለ ክርስትና ሃይማኖት ቀናዒ በመሆን የጣዖት ምስሎች እና መቅደሶች እንዲፈርሱ እና አብያተ ክርስቲያናት ተሰርተው በውስጣቸው ቅ/ሥዕላት ይሣሉ ዘንድ አዝዞ ነበር።
- *በቤተክርስቲያን ታሪክም የቅዱሳት ሥዕላት አገልግሎት በሰፋት አብቦ መታየት የጀመረው የቤተክርስቲያን ሰላምና ነጻነት ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ነው።*

ቅዱሳት ሥዕላት
በኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ

ቅዱሳት ሥዕላት በኢትዮጲያ አ/ተ/ቤ/ክ
Axumite period

- በ4ኛው መ.ክ.ዘ. ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አብሮም ወጥ በሆነ መልኩ የመጻሕፍት አጻጻፍ እንዲሁም የአውሳብዮስ የቀኖና ሰንጠረዥና የያዛቸው ጌጣጌጦች ትናንሽ የወንጌላውያን ቅዱሳት ሥዕላት መሣል አብሮ ወደ ሀገራችን መጣ። ለምሳሌ፡-
  - የአባ ገሪማ ገዳም የሚገኙት የወንጌል መጽሐፍት ገሪማ ፩ እና ፪ [Garima 1 and 2]
    - *THE ART NEWSPAPER. Research uncovers lost African school of painting፡ Analysis of illuminated gospels suggests that first Christian manuscript art may have come from Ethiopia. Number 252, December 2013. Alessandro Bausi. Ethiopia and the Mediterranean World in Late Antiquity: The Garimā Gospels in Context. Alessandro Bausi, "The 'TrueStory' of the Abba Gärima Gospels", COMSt Newsletter 1, 2011, p. 17–20.Earliest Christian Manuscript: Illuminated Art in Garima Gospels* http://www.decodedpast.com/garima-gospels-earliest-christian-manuscript /4358 .

Axumite period . . .






Axumite period . . .

- ታባሪ (Tabari) ኡም ሀቢባ
  - ወደ ሀገሯ ስትመለስም ለዓረብ ዜና መዋዕል ጸሐፊያን በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ስለተመለከተቻቸው ቅዱሳት ሥዕላት በተደጋጋሚ አድናቆት በተሞላበት ንግግር ተናግራለች።
    - Jules Leroy. Ethiopian paintings in the middle ages.62. Paul B. Henze. layers of time: A history of Ethiopia.36

Zagwe Period መ.ክ.ዘ.



Early Solomonic Period



Early Solomonic Period. . .



Early Solomonic Period. . .




Late Solomonic Period

የመጀመሪያው የጎንደር አሣሣል ዘይቤ



Late Solomonic Period . .

ሁለተኛው የጎንደር አሣሣል ዘይቤ



20ኛው እና 21 መ.ክ.ዘ.



4. የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማና ጥቅም

ቅዱሳት ሥዕላት



ጥቅም



ዓላማ



የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማ

1. ማስተማር

ትምህርተ ሃይማኖትን

- የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እንደተጠቀሙበት
- ሉቃውንት የቅዱሳት ሥዕላትን ሃይማኖታዊ ሚና “ሥዕላዊ ነገረ እግዘአብሔር ወይም ሥነ መለኮት /**Theology in Imagery/**” በማለት የሚያስተምሩት።

የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማ . . .

ክርስቲያናዊ ሥነምግባርን

- **የዘፈን ጉዳትን** የቅ/ዮሐንስ አንገት እንዳስቆረጠ በመጠቆም
- የይስሐቅ መሥዋዕትና መታዘዝ **እናት አባት ማክበርና መታዘዝን** በማስተማር
- ጌታ ሕብስቱን ሲባርክ **ከምግብ በፊት ጸሎት** እንደሚገባ ወዘተ. . .
- የቅዱሳን አለባበስ እና የአዳምና ሔዋን እርቃን መሆን **ክርስቲያናዊ አለባበስ**

የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማ. . .

ታሪክን

- በተለያዩ ዘመናት የተከናወኑትን ዐበይት ታሪኮችን ቅ/ሥዕላት ያስተምራሉ፡፡
  - ለምስል በአፄ ገ/መስቀል ዘመን ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደምጣ ይተርካሉ፡፡
  - አፄሚኒሊክ በቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት ተማፅነው የሀገር እና ሃይማኖት ድንበር ሊያፈልስ ሊወር የመጣውን የጣልያንን ጦር በአድዋ ጦርነት ድል እንደነሱ፡፡

የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማ. . .

2. ለሥርዓተ አምልኮ

- ለጸሎት እና አስተብርኮ
- ምዕመናን በተመስጦ ለመጸለይ ስለሚረዷቸው
- ከቅዱሳን ሕብረት በመንፈስ የምንገናኝባቸው ድልድዮች ወይም መስኮቶች በመሆናቸው “ *ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላጋሮች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።*“ (ኤፌ 2፡20) (1ኛ ዮሐ 1፡1-3)

የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማ . . .

3. ፍቅርን ለመግለጽ እና ለማሰብ

- አንድ ሰው የቤተሰቦቹን ፎቶ በአጠገቡ እንደሚያኖርና እንደሚስመው

"ከመ ይትፌሳህ ሕጻን ሶበ ይሬኢ እሞ፤እትፌሳህ እንሰ ሥዕልኪ በርዕይ ወበተሳልሞ፤ሕጻን ልጅ እናቱን ባየ ጊዜ ፈጽሞ ደስ እንዲሰኝ ሥዕልሽን በማይበትና በምሳለምበት ጊዜ ደስ እሰኛለሁ።"

የቅዱሳት ሥዕላት ዓላማ. . .

4. በሥዕል የተገለጹትን ቅዱሳን በሕይወታቸው እንድንመስላቸው ማበረታታት

- ለምሳሌ አንድ ሰው አቡነ ተክለሃይማኖት ለሰባት ዓመት በአንድ እግራቸው ቆመው መጸለያቸውን የሚያሳየውን ሥዕለ አድኅኖ ሲመለከት “አርሳቸው ሰባት ዓመት ቆመው ከጸለዩ እኔ እንዴት ሦስት ሰዓት ቆሜ ማስቀደስ ያቅተኛል” በማለት ለጸሎት እንዲተጋ መንፈሳዊ ሰንቅ እንዲይዝ ብርታት ይሆኑታል ማለት ነው።
- *Basil the great*

የቅዱሳት ሥዕላት ጥቅም

መንፈሳዊ

ዓለማዊ

መንፈሳዊ

- ለሥርዓተ አምልኮ ማስፈጸሚያነትና
- ለማስተማርያነት።
- ሃይማኖታዊ ምስጢሮችን ዘወትር በማስታወስ
- ምዕመናን በጭንቀታቸውና በችግራቸው ጊዜ በእምነት ሆነው በሥዕላቱ ፊት ሲጸልዩ ተአምራትን በመፈፀም የማዳን አገልግሎት መስጠት . . .

ዓለማዊ (Secular)

- በተለያዩ ዘመን ለተነሡት ለኢትዮጲያውያን ሠዓሊያን የሥዕል ጥበብን እንዲማሩ ምክንያት ሆነዋል።
- ለኢትዮጲያውያን ማኅበራዊ አገልግሎትን ባለፉት ዘመናት ሲሰጡ ቆይተዋል።
  - *«ኩራተ ርዕሱ»*
- ከሥዕላቱ በመነሣት በተለያዩ ዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ታሪክ፣ ሕይወትና መስተጋብር መገመት ይቻላል።
- ወደ ሀገራችን የቱሪስት ፍሰትን በመሳብ እና በመጨመር ቅዱሳት ሥዕላት ለቤተክርስትያን እና ለሀገራችን ትልቅ የገቢ ምንጭ ናቸው።


ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር